፥

ፓኖራማ ቁጥር 68

የትዝብት አድማስ

ሚያዚያ 18 ቀን 2001

## የጠባቦች የካርታ ጨዋታ ሲፈርስ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ሲነግሥ !

ኢትዮጵያ ሀገራችን ተፈጥሮ ካደላት በርካታ ፀጋዎች መካከል ዓይነተኛውና መሠረቱ፥የብዙ ብሔር ብሄረሰቦች ሀገር መሆኗ ነው። ይህ ገፅታዋ ደግሞ ዜጎቿን የሀገሪቱ ልዩ የውበት አክሊልና ፈርጥ አድርጓቸዋል ። የአንድ ሀገር ሕልውናው ፥ ሕይወቱና ማንነቱ ደግሞ የሚወሰነው በዜጎች መኖር ለመሆኑ ማንም ሊከራከር አይችልም ። ከፖለቲካና ከህግ ትርጉምና አገላለጽ አንፃር ሲታይ ደግሞ ፥ሀገርን ሀገር ከሚያሰኙት መሠረታዊ መስፈርቶች ሦስት ጉዳዮች ተሟልተው ሲገኙ እንደሆነ ታውቆ የተመዘገበ ነው ። እነርሱም፥

1ኛ. ዳር ድንበሩ በህግ የታወቀ መሬት፥ / የግዛት አንድነት፥

2ኛ. በዚህ የግዛት አንድነት ላይ የሚኖሩ ዜጎችና፥

3ኛ. የሁለቱን መስፈርቶች ተቀብሎ አክብሮና የዜጎቿንም ተዓመኔታና አፅድቆት ያገኘ መንግሥት ናቸው ።

ባጭሩ፥ አንድ ሀገር የነኝህ ሦስት ነገሮች ድምር ውጤት ነው ማለት ይቻላል ። በዘመናት፥በማንኛውም ሀገር የሚፈራረቁ አገዛዞች/ መንግሥታት እንደነበሩና እንዳሉ ሁሉ፥ በሀገራችንም ተፈራርቀዋል ። ይህም ከፊውዳል አገዛዝ ጀምሮ ፥ የአምስቱን ዓመት የኢጣሊያን ወረራን ጨምሮ ፥ ፋሽስታዊ የደርግ አምባገነንና የወያኔን ዘረኛ ሥርዓትን ያጠቃልላል ። ከወቅቱ የወያኔ ጎጠኛ ቡድን በስተቀር ቀደም ያሉት ወደ ታሪክ ቆሻሻ ተወርውረው ቀርተዋል ። በኢትዮጵያ ያርበኝነት ትግል ! ዘረኛው ሥርዓትም ተራውን ጠብቆ ወደ ከርሰ-መቃብሩ መውረዱ አይቀሬ ነው። የወያኔን ቡድን ከእርሱ በፊት ከነበሩት

ሁለት ሥርዓቶች ባያሌው ከሚለይቱ ዋናዋና ጉዳዮች አንዱ÷ስለ ሀገሪቱ የግዛት አንድነትም ይሁን ስለዜጎቿ አብሮ መኖር "እኔን የሚያገባኝ ጉዳይ አይደለም " ማለቱ ነው ። ይህ ደግሞ እርሱ ራሱም ወያኔ ቢሆን የማይክደው ሃቅ ሆኗል ። በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ÷ ሀገርን ሀገር ከሚያሰኙት መሠረታዊ አካላት አንዱ÷ መንግሥት የሚባለው ክፍል እንደሌለ ማንም ሊከራከር አይችልም÷ " ሲራክ በምግባሩ ÷ ጠፋ መቃብሩ" እንደተባለው÷ ይህ እኩይ የወያኔ ዘረኛ ሥርዓትም ወደ ከርሰ- መቃብሩ ተደፍቶ እንደሚቀር ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳችም ጥርጣሬ አይኖረውም ። በሀገራችን በኢትዮጵያ አንድ አባባል አለ። " በቀልን ስትፈለግ ሁለት መቃብሮችን መቆፈር ሊኖርብህ ነው ። አንደኛው ያንተ የራስህ መቃብር ነውና! " መለስና ግብረ-አበሮቹ ከፍርሃት÷ ከጥላቻና ከበቀል ተነስተው የኢትዮጵያን ሕዝብ መቃብር ሲቆፍሩ ያድራሉ። ታዲያ ይህንን በትዝብት የሚመለከተው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ÷

" አትዋል ይዋሉብህ÷ ክፉ አትምከር÷ እነርሱ ይምከሩ"
በቆለሉት አፈር ÷ በቆፈሩት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ÷
ወያኔም ተቀብሮ ድራሹ ሲጠፋ÷ ታሪኩ ይጠፋል እስከ መቃብሩ። "

በማለት ዜና-መዋዕሉን እየመዘገበ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሕዝብ÷ እንደማንኛው ሀገር ሕዝብ ሁሉ÷ በማንኛው ጠላቱ ላይ ፍትህ-ርትዕን እንጅ÷ የበቀል እርምጃ ወስዶ አያውቅም ። በቀል የፈሪዎችና የደካሞች ባኅርይ ስለሆነ÷ ጀግና ሕዝብና የታላቅ ሀገር ዜጋ በቀልን አንግቦ ለመኖር ሲያልፍም አይነካው ። ይህ አባባል እንዲያው ለነባቢት ተብሎ የሚነገር ሳይሆን ÷ በታሪክ ተደጋግሞ የተገለፀ ነው ። ለዓብነት ያህል ÷ አንድ ሁለቱን ጠቃቅሰን እናልፋለን። በ1888 ዓም ሀገሩን ሊወርበት የመጣውን የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት ጦር በአድዋ ጦርነት ድባቅ ከመታው በኋላ ምርኮኛውን እንዲከበብ አደረገ እንጅ የበቀል እርምጃ አልወሰደበትም ። አንድም የኢጣሊያ ምርኮኛ አልተነካም ። እንዲያውም በውሃ ጥም እንዳያልቅ ታስቦለት÷ በአካባቢ የነበሩትን የውሃ ጉድጓዶች እንዲጠቀም ተፈቅዶለት ነበር ይባላል። ለዚህም ነበር የወቅቱ ዜና-መዋዕል÷

" ጣሊያኑ ተከብቦ ውሃ ውሃ ሲል÷ ስጠው አለ ጻኘው ሠላሳ በርሜል። "

ሲል የመዘገበው። ከዚህም በቀር ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ÷ የኢጣሊያን ሕዝብ እንደ ሕዝብ ጠላቴ ነው ብሎ አያውቅም። በአርባ ዓመታት የጊዜ ክልል በአድዋና ማይጨው ወራራ

እንዲካሄድበት ያደረጉት ሁለት የኢጣሊያ መሪዎች ማለትም÷ጠቅላይ ምኒስትር ክርስፒንና ዱቼ ሙሶሊኒን እንዲሁም የቅኝ ግዛዥዎችን ድፍረትና ድርጊት እንጅ÷የኢጣሊያንን ሕዝብ እንዳለ በጠላትነት አልመዘገበም ። አይመዘግብምም ። የመቅደላው ታሪካዊ ክስተትም ተመሳሳይ ታሪካዊ ዶሴ ነበር ያስመዘገበው ። የእንግሊዝን የቅኝ ገዥዎች ድፍረትና ምኞት አዋርዶ ከመስደድ በቀር÷ የእንግሊዝን ሕዝብ እንደ ሕዝብ በጠላትነት ፈርጆ ለበቀል አያስብም ። አለመታደል ሆኖ እንደሆነ አናውቅም÷ የዛሬዎቹ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ግን አሁንም የትላንቱን ቂማቸውን አልተውም ። ለአገልጋያቸው ለወያኔ ሙሉ ድጋፍ እየሰጡ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሪር ሀዘን ውስጥ አስገብተውታል። የእንግሊዝና ሌሎች ምዕራባውያን መሬዎች÷በማያገባቸው÷ባልቸገራቸው÷በማያውቁትና ባልተረዱት በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ በመግባት ÷ በኀንለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም እጃቸውን ነክረዋል። ሀገራችንን ለመገነጣጠል አሲረዋል ፤ተረባርበዋል ። ያም ሆኖ ግን÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሪዎቹ ላይ መሪር ሀዘኑን ከመግለጽ እልፍ ተርፎ በመሚሯቸው ሕዝቦች ላይ የጥላቻ መንፈስ የለውም። ምክንያቱም÷መንግሥትን ከሀገር ÷መሪዎችን ከሕዝብ ለይቶ የማወቅና የመፈረጅ ዕውቀትና ተመክሮ ስላለው ነው ። ዕውነቱን አፍረጥርጦ መናገር ያስፈልጋል ከተባለ÷ የሀገራችንን ስር የሰደደና ውጥንቅጡ የወጣን ብሔራዊ ችግር ፤እንኳንስ ባዕዳን ÷ እኛም ዜጎቿ ብንሆን የቱን ያህል ጠንቅቀን እንደምንረዳው አፍ ሞልቶ መናገር ያስቸግራል ። ያማ ባይሆን ኖሮ ÷ መፍተሄውን ማግኘት ባልቸገረንም ነበር። ለዚህም ይመስላል÷የባዕዳንን በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ መግባትንና መፍተሄውን እኛ እንስጣችሁ የሚለውን ዝባዝንኪ በመቃወም የኢትዮጵያ ሕዝብ የትዝብት እንጉርጉሮ የሚያሰማው።

> “ ለእኔም አልሆነልኝ ለድሃ ዜጋይቱ÷ ለጦም አደሪቱ÷ መከራ ደስታውን ሁሉን ታዛቢቱ÷
> በይ ገብተሽ ሞክሪው ÷ በቆም ጨልጢቱ÷ በይ ቀምሰሽ ፈትኝው ደፋፍተሽ ሀጅቱ ። ”

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዘመናቱ የሚመጡትን የባዕዳን ወራሪ መንግሥታትና ሕዝብ ለይቶ መፈረጅ ከቻለ ደግሞ ÷ የሀገር ውስጥ ጨቋኞቹን ለመረዳት የሚሳነው ሕዝብ አይደለም ። በመሆኑም÷በምንም ዓይነት የፖለቲካ ትንታኔም ይሁን የታሪክ ተዛማች አጋጣሚ÷የወያኔን ብሔራዊ ወንጀልና ሀገራዊ ጥፋት ከትግራይ ሕዝብ ጋር አያይዘውም።የትግራይ ሕዝብም በበኩሉ÷ ስሜን ተጠቅሞ ምኒሊክ ግቢ ገብቷል በሚል ብቻ÷ የነመለስን ብሔራዊ ወንጀል ተቀብሎ ጎሽ ልጆቼ ብሎ የደገፋቸዋል ብለን ማመን አንፈልግም።ሁሉም ዜጋ÷ የትግራይን ሕዝብ ከወያኔ÷ ወያኔን ደግሞ÷ ከድርጅቱ መሪዎች ከነመለስ ዜናዊ ለይቶና ፈርጆ-አመዛዝኖ የራሱን ትክክለኛ ድምዳሜ ለማድረግ የሚያስችለው የፖለቲካ ንቃተ-ኀሌና አለው ። ራሳቸውን ከወያኔ ጋር የሚፈርጁ የትግራይ ምሁራንና ተወላጆችም ቢሆኑ ÷

ራሳቸውንም ሕዝብንም ለጥፋት ሰለባ እንዳይዳርጉ ማሰብ አለባቸው ፡፡ ዕብሪተኛው ወያኔ ዕድሜው እያጠረ እንጂ እየረዘመ የሚሄድ አይደለምና ፡፡ በወተር፥ በአርባ ጉጉ ፥ በአርባ ምንጭ፥ በደብረ ብርሃን፥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ፥ በጎንደር አደባባይ-የሱስ ምዕምናን ፥ በአዲስ አበባ መስጊድ ምዕመናን ፥ በጋምቢላ ዜጎችና በሌሎቹም ቦታዎች ቁጥራቸው በትክክል የማይታወቁትን ዜጎች የጨፈጨፈና ያስጨፈጨፈ ፥ ወያኔና ነፍሰ - ገዳዩ የዓጋዚ ቡድን እንጅ፥ የትግራይ ሕዝብ እንዳለሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል ፡፡ ጋይምን ፥ አሰፋ ማሩን ፥ ፕሮፌሶር አሥራት ወ / የስን ፥ ተስፋዬ ታደስን ፤ አንጋፋውን የኢትዮጵያን መምህራን ማኅበር መሪ ብርቅየውን መምህር አቶ ከበደ ደስታን፥ሌሎችንም አሰቃይቶ ያስገደለ መለሰ ዜናዊ እንጅ፥ የወንጀሉ ድርጊት ከትግራይ ሕዝብ ጋር ጨርሶ የሚያያዝ አይደለም፡፡ ታዲያ የወያኔን ድርጊት የተቃወመውን ሁሉ በትግራይ ሕዝብ ላይ እንደመዝመት ነው እያለ ሰሞኑን በአጫፋሪዎቹ መድረኮች ላይ ተቃዋሚውን ሁሉ በትግራይ ሕዝብ ላይ እንደተነሳ አድርጎ የሚያሰራጨው ርካሽና ኃላፊነት የጎደለው የጥላቻ መርዝ፥ ከከፋፋይና ጠባብነት ካርታ ጨዋታ የሚያልፍ አይደለም ፡፡ ይህ ደግሞ ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ሙሉ ተጻጭሮ ተጻጭሮ ሁሉን ያሰለቸ ፍሩሽካ ሆኖ ቀርቷል፡፡

ኢሕአፓ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጋፋ ፓርቲ እንደመሆኑ፥ አመሠራረቱ ፥ አባላቱ፥ ይዘቱ፥ አደረጃጀቱ፥ አሰራሩ፥ ራዕዩና ሀገራዊ ቃል-ኪዳኑ፥ ህብረ ብሔራዊና ኢትዮጵያዊ ነው ፡፡ ከመስራች አባላቱ ጀምሮ አመራር-አካላት - አባለቱ ተሰባስበው እየታገሉና ያን ሁሉ መሥዋዕት የከፈሉትና አሁንም በመክፈል ላይ የሚገኙት ፥ ለመላዋ ኢትዮጵያና ለዜጎቿ ብሔራዊ ጥቅም መሠረት የሚሆነውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ለማስፈን ነው ፡፡ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም እየሸራረፉ ፥ በየጎጥና ክልል ባላዎች እየተንጠላጠሉ ፥ ሀገራዊ ዋልታውንና ምሶሶውን እየገዘገዙ-እየከረከሩ ለመሄድ፥ የቆሙበት ዓላማና የገቡበት ቃል ኪዳን አይፈቅድላቸውም፡፡ ለሀገራቸውና ለዜጎቿ የሚገለጹት ፍቅር፥ ለግል ጥቅምና ለከንቱ ውዳሴ አይደለም፡፡ በመሆኑም ፥ እንደ ጠባቦቹ ፥ ወያኔዎች ፥ ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ ሊሉ አይችሉም ፡፡ የኢሕአፓ ታጋዮች ፥ ኢትዮጵያን የሚያይዋት ፥ ዛሬ ከገጠሟት ችግሮች አኳያ ብቻ ሳይሆን፥በእኩልነት ላይ የተመሠረተውን የዜጎቿን አንድነት አክብራ ወደልማት ጎዳና የምታመራውን የነገዋንም ኢትዮጵያን ጭምር ነው ፡፡ ዛሬ የወያኔ መሪዎች በብሄረሰብ፥ በሃይማኖትና በቋንቋ ልዩነት ላይ የሚያናፍሱት የጥላቻንና የበቀልን መርዝ ማስወገድ ፥ የኢሕአፓ የነገ ኃላፊነት ነው ብሎ ቅድሚያ ሰጥቶታል ፡፡ አድሎና ሙስና ፥ የሌለበት ፥ የሁሉም ዜጋ ስብዓዊ መብትና ነፃነት በህግ የሚከበርበት፥ፍትኅ-ርትዕና የህግ የበላይነት የሚሰፍንበት፥መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍል ኃላፊነትና ተጠያቂነት፥የመልካም አስተዳደር መሠረት የሆነባት ሀገር መመስረት የኢሕአፓ

ራዕይ ነው ፡፡ይህ ደግሞ ምኞት ሆኖ የሚቀር ሳይሆን ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመተባባር ቁርጠኛ ትግልና መስዋዕት በመክፈል የሚሳካ ይሆናል ፡፡የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ድጋፍና ትብብር ያካተተ ትግል ደግሞ ፥ ለሁሉም ዜጋ ተጠቃሚነት ዋስትና ይሆናል እንጅ ፥ወያኔ አሁን የጠባብነት ካርታ እየተጫወተ እደንሚያራምደው መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ የትግራይን ሕዝብ ለእልቂት የሚዳርግ ሊሆን ከቶ አይችልም ፡፡ የወያኔ መሪዎች ፥ ልክ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ሁለት ሥርዓቶች ሲጠቀሙበት እንደነበረው ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ለመጠቀም መሞከራቸውን ፥ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ተረድቶታል ፡፡ የአፄው ሥርዓት ተቃዋሚዎቹን ሲያጠፋ የነበረው ፥ በሰሎሞዊ ዙፋን ስር ጸንቶ የኖረውን ሕዝብ ሰላማዊ ኑሮ ለማናጋት ይል ነበር ፡፡ ደርግም በበኩሉ ፥ አብዮቱን ለመቀልበስ ያሴረ ነው በሚል ስንቶቹን ንፁኃን ዜጎች እንደጨፈጨፈ የቅርብ መሪር ትዝታችን ነው ፡፡ ዛሬም ወያኔዎቹ በሥልጣናቸው ለመቆየት ያስችለናል ብለው የሚጠቀሙበት ፥ የጠባብነት ካርታ ጨዋታ ሆኗል ፡፡ ይህ የነፈሰበትና የከሰረ የዘረኛ ፖለቲካ ግን በማነኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ቀርቶ ፥የአልፎ ሃጅ ጆሮ እንኳን አያገኝም ፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ፡-

**<u>“ የዘረኞች የካርታ ጨዋታ ሲጠፋ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ሲፋፋ ! ”</u>**

**የምንለው!**